# ከሽብር ተጠሪጣሪው የእምነት ቃል በስተጀርባ

**አቡበከር አባፊጣ-ከላፍቶ**

ነገሩ አስገራሚ ነው– ከመሰንበቻው የሰማነው የጅሃድ ተጠርጣሪው ግለሰብ የእምነት ቃል፡፡ የቃሉ ቅንጭብታም እንዲህ የሚነበብ ነው – " ብር ቢላክልኝ ኖሮ፤ የእምነት ውስጥ የውጊያ ስልጠና ልሰጥ ነበር" በሚል፡፡ ይህ አባባል ከአል -ሸባብና እና ከአል-ቃዒዳ ጋር በመገናኘት ሀገራችን ውስጥ የጀሃድ ጦርነትና የሽብር እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ነበር በሚል ክስ ሰሞኑን ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳያቸው መታየት ከጀመረው አሰራ አንድ ተካሳሾች ውስጥ የአንዱ ነው፡፡

ግለሰቡ ሐሰን ጃርሶ ይባላል፡፡ የኬንያ ዜግነት ያለውና ሶማሊያ ውስጥ ይኖር የነበረው ይህ ግለሰብ፤ በቁጥጥር ስር ከዋሉት አምስት ተከሳሾች መካከል የመጀመሪያው ነው፡፡ 'ወንጀሉን ፈጽመሃል ወይ?' ተብሎ ከፍርድ ቤት ለቀረበለት የእምነት ክህደት ጥያቄ 'ለመፈጸም አስቤ ነበር፤ ነገር ግን ተግባራዊ አለሆነም" የሚል ምላሽ የሰጠው ተጠርጣሪው፤ "አል - ሸባብ" እያለ ራሱን የሚጠራው አሸባሪ ቡድን ቅርንጫፍ የሆነው "ማህጅሬ" የተሰኘ ድርጅት አባል መሆኑንም ባይፋ ገልጿል፡፡ እንደ ተካሳሹ የእምነት ቃል፣ አብዱራህማን በሚባል ሰው አማካኝነት ከውጭ ገንዘብ ሊላክለት እንደነበርና በኢትዮጵያ መንግስት ላይም ውጊያ ለመክፈት አስቦ ነበር፡፡ ይሁንና ገንዘቡን ባሌ-ሮቤ ላይ በመጠባበቅ ላይ ሳለ በህዝብና በፀጥታ ኃይሎች ትብብር በቁጥጥር ስር መዋሉን ለፍርድ ቤት አስረድቷል፡፡

መቼም ውድ አንባቢዎቼ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የተጠርጣሪዎቹን የፍርድ ቤት ውሎ ለእናንተ ማቅረብ አለመሆኑን እንደምትገነዘብልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱን አስገራሚ ጉዳይ መስማታችሁ ስለማይቀር ነው፡፡ እናም የጽሑፌ አነሳሽ ምክንያት ከሽብር ተጠርጣሪው የእምነት ቃል ባሻገር ያሉትን የአክራሪነት ዕውነታዎች ማሳየት ነው፡፡

እርግጥም ከተከሳሹ ግለሰብ የ"ወንጀሉን ፈጽሜያለሁ" የእምነት ቃል በስተጀርባ አንድ ሃቅ ፍንትው ብሎ ይታያል፡፡ ይኸውም ሃይማኖትን እንደ መከላከያ ምሽግ በመቁጠር፤ ጥቂት ግለሰቦች የፖለቲካ ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ ሀገራችን ውስጥ የአክራሪነትንና የአሸባሪነትን አጀንዳዎች በማንገብ ብቅ ጥልም እያሉ መሆናቸው ነው፡፡ ታዲያ ይህን መሰሉን በሃይማኖት ሽፋን በሚከናወን ትርምስ ውስጥ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በህቡዕ የሚካሄድ ፀረ -ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴን ህዝብና መንግስት በጋራ "ሳይቃጠል በቅጠል" ሊሉት ይገባል፡፡

ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ይህ ነው የሚባል የአክራሪነትና የአሸባሪነት ስጋት በሀገራችን ውስጥ የማይታይ ቢሆንም፤ በተለያዩ ጊዜያት እያቆጠቆጡ ወዲያወኑ የሚከስሙ ተግባራትን መቆጣጠርና መመከት የግድ ይላል፡፡ ለምን ቢባል፤ ሃይማኖትን እንደ ግርዶሽ በመጠቀም የሚከናወኑና ግባቸው ፖለቲካዊ የሆኑ የሽብር ፍላጎቶች በዋነኛነት በህዝብና በሀገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳቸው አይቀሬ በመሆኑ ነው፡፡ ታዲያ

እዚህ ላይ ‘ለመሆኑ እንደ እነ ሃሰን ጃርሶ ዓይነት የሽብር ተጠርጣሪዎች ዓላማቸውን ቢያሳኩ ምን ይፈጠር ይሆን?’ የሚል ጥያቄን ማንሳት ያስፈልጋል።… ጥቂት ነጥቦችን በማውሳት የአደጋውን ግዝፈት እንደሚከተለው መቃኘት ይቻላል፡፡…

በአክራሪነትና አሻበሪነት ሳቢያ ከሚፈጸሙ አደጋዎች ውስጥ በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ጅምላ ጭፍጨፋዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው ተግባራቱ በባህሪያቸው ንጹሃን ህዝብን ዒላማ የሚያደርጉ በመሆናቸው፤ ዳፋው የሚተርፈው ከድህነት አዙሪት ቀለበት ወጥቶ ራሱንና ሀገሩን ለመለወጥ ደፋ ቀና በሚለው ሰላማዊ ዜጋ ላይ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ በርካታ አብነቶችን መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም፤ የአንድ ወቅት ሁኔታን ብንመለከት እንኳን በኦነግ ወይም ኦነግ በነበሩ ሰዎች አማካኝነት “ሃዋርጅያ” የተባለ የሙስሊም አክራሪዎች የተቀመረ የጥፋት እንቅስቃሴን ማውሳት ይቻላል፡፡ በወቅቱ እነዚህ ወገኖች በብሔር መብት ዙሪያ ያካሄዱት እንቅስቃሴ ሃቁን በሚገነዘበው ህዝብ ተቀባይነት በማጣቱ፤ ማርሻቸውን ወደ ሃይማኖት በመቀየር በምዕራቡ የሀገራችን ክፍል በርካታ ዜጎች ለህልፈተ-ህይወት እንዲዳርጉ እንዲሁም ቤት ንብረታቸው እንዲወድም አድርገዋል፡፡ ምንም እንኳን ይዘውት የተነሱት ዓላማ በህዝቡ ርብርብ ቢከሽፍም፤ ይህን መሰሉ በሃይማት ሽፋን የሚደረግ የፖለቲካ ሩጫ በዋነኛነት የሚጎዳው ህብረተሰቡን መሆኑን አመላካች ትውስታ ጥሎ አልፏል፡፡

በዚህ ረገድ በኦርቶዶክስ እምነት ውስጥም የከሰሩ ፖለቲከኞችን ዓላማ የሚያራምዱና በካህን ልብሳቸው ፖለቲካዊ ተግባራትን ሲያከናውኑ የነበሩ አባላቶችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በምርጫ 97 ወቅት አንዳንድ አሜሪካ የሚገኙ ጳጳሳት “ቅንጅት” የተሰኘው የነውጥ ቡድን በጠራው ሰልፍ ላይ ከመገኘት አልፈው፣ በአስተባባሪነት የአባትነት ካባቸውን ለብሰው መገኘታቸው በሃይማኖት ጥላ ስር የፖለቲካ አጀንዳ እንዴት እንደሚከናወን አስረጅ ይመስለኛል፡፡ በሌሎች ሃይማኖቶችም ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እንደሚፈጠር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

የአክራሪነትንና የሽብርተኛነትን አደጋዎች ከሀገራችን አኳያ በሌላኛው የጥፋት ዘውጋቸው ስንመለከታቸው፤ የተጀመሩና በማበብ ላይ የሚገኙ የልማት ትልሞችን የሚያቀጭጭ መሆኑን ለመረዳት አይከብድም። ተጠርጣሪው ግለሰብ “ብር ቢላክልኝ ኖሮ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የውጊያ ስልጠና ልሰጥ ነበር” በማለት ለፍርድ ቤቱ የሰጠው ቃል የሚያመላክተው ነገር ቢኖር፤ ስልጠናውን ከሰጠ በኋላ በሚያፈራቸው ተከታዮቹ የሀገሪቱን ሰላም ማወክ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሰላም ከሌለ ስለ ልማትና ዴሞክራሲ ማሰብ አይቻልም፡፡ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት የተፋጠነ ልማትን ለማምጣት መንግስት ትክክለኛ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይዞ ውጤት እያመጣ ቢሆንም፤ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ከሌለ እንቅፋት መፈጠሩ አይቀሬ ነው፡፡

በሀገር ውስጥ በሃይማኖት ግጭት የሚታመስ ማህበረሰብ ስለ ልማት ሊያስብ አይችልም፡፡ የዜጎች ካፒታልና ጉልበት በሰላማዊ ሁኔታ ካልተንቀሳቀሱ ደግሞ የሀገርን ዕድገት ሊያረጋግጡ አይችሉም፡፡ ከውጭ የሚመጣው ባለሀብትም ቢሆን አስተማማኝ ሰላም ከሌለ ማፈግፈጉ አይቀርም፡፡ በድምሩ ሲታይ በሀይማኖት

ሰበብ የሚከናወኑ ማናቸውም ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ተግባራት የሀገራችንን የመልማት ብሎም የህዝቦቿን የተጠቃሚነት ዕድል በአያሌው የሚገደብ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የእነ ሐሰን ጃርሶ የጥፋት እንቅስቃሴም የሚያስረዳን ዕውነታ ይህንኑ ነው፡፡

የእነ ሐሰን ጃርሶን እኩይ ፍላጎት በሀገራችን በመካሄድ ላይ ከሚገኙት የሰብዓዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶች አመርታ እንቅፋትነት አኳያ ልናየው እንችላለን፡፡ የግለሰቡ የእምነት ቃል እንደሚያስረዳው ግለሰቡ ቢሳካለት ኖሮ፤ ሃሳቡ ሰዎችን አሰልጥኖ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ላይ ጦርነት መክፈት ነው፡፡ ይህ አባባል የራስን እምነት በሌሎች ላይ በሃይል የመጫን ኢ-ሰብዓዊና ፀረ-ዲሞክራሲያዊ እሳቤን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠርጣሪው በሚያስበው መልኩ ሁኔታዎች ቢሟሉ፤ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፤ የመከራከርና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የመሸናነፍ ዕድል ከነ አካቴው ይጠፋል፡፡ ሰዎች መብታቸውን ጉልበተኞች በሚሰጧቸውና በሚነፍጓቸው ልኬት መጠቀም ይጀምራሉ፡፡

የተጠርጣሪው ዓይነት ግለሰቦች መብት ሰጪና ነሺ ሆነው መልካም አስተዳደርን መደፍጠጣቸው አይቀርም፡፡ ይህም ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያገኙትን ስልጣን በፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ለማግኘት ዕድሉን ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታም የእነ ሐሰን ጥያቄ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ እምነታቸው "ጅሃድ" በሚል የሃይል አመለካከት የህዝብን ስልጣን በጉልበት መያዝ በመሆኑ፤ በሚቆሰቁሱት የእሳት ቋያ ለህልፈተ-ህይወት የሚዳረገው ወገን፣ የሚጠፋው ንብረትና የሚገታው የሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ለእነርሱ ግምት ውስጥ የሚገቡ አይደሉም፡፡ ታዲያ በእንዲህ ዓይነት የለየለት ፀረ-ህዝብ ተግባር የሚገኝ ስልጣን መልሶ ህዝቡን እንደ እግር እሳት የሚለበልብ መሆኑን ከጎረቤታችን ከሶማሊያ መማር እንችላለን፡፡

በቅርቡ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እንደተመለከትነው፤ ወንድም የሆነው የዚያች ሀገር ህዝብ፤ በአል-ሸባብ ኢ-ሰብዓዊና ፀረ-ዲሞራሲያዊ አገዛዝ ስር በነበረበት ወቅትና ነፃ ከወጣ በኋላ ልዩነቱን የገለፀው ቀዳሚ ጊዜውን "አልኖርኩም" በሚል ነው፡፡ እርግጥም በገዛ ህዝቡ ላይ "ጅሃድ" አውጆ በተለያዩ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ስልጣን ይዞ የነበረው የሽብር ቡድኑ፤ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ጨፍልቋል። ለምን ፊልም ተመለከትክ፣ ሙዚቃ ያለበት ቴሌቪዥን አየህ፣ ጫት ቃምክ በማለት ህዝቡን ቁም ስቅሉን አሳይቶታል፡፡ ለዚህም ነው የሶማሊያ ህዝብ በአል-ሸባብ አገዛዝን የገሃነም-እሳት ያህል በመቁጠር በይፋ "ውግዝ ከመአርዮስ" እያለ በምሬት ተንገሽግሾ የሚናገረው፡፡

እንግዲህ የአል-ሸባብ አንድ ክንፍ መሆናቸውን የነገሩን እነ ሐሰን ጃርሶ ገንዘብ ቢላክላቸው ሀገራችን ውስጥ ሊያመጡት የሚፈልጉት የፖለቲካ አስተሳሰብ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተጠርጣሪው ራሱ በፍርድ ቤት ውሎው "ማህጀሬ" በሚባል ድርጅት ውስጥ "ሙጃሃዲኖች" የሚሰኙ አክራሪዎችን በመመልመል የአል-ሸባብን ፈለግ እንደሚከተል በመግለፁ ነው፡፡ ታዲያ ይህን መሰሉን የግዴታ ሃይማኖታዊ ፖለቲካን ለመጠቀም የሚሹ የከሰሩ የውስጥና የውጭ ኃይሎችን ሁላችንም በምሬት ልንታገላቸው የሚገባ ይመስለኛል፡፡

ተጠርጣሪው ግለሰብ “ባሌ-ሮቤ ላይ ገንዘብ ከውጭ ስጠብቅ ተያዝኩ” የሚለው አባባሉ አንድ ፍንጭን የሚጠቁም ይመስለኛል፡፡ ይኸውም በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የራሳቸውን ፍላጎት ሀገራችን ውስጥ አክራሪነትን ማራመድ የሚሹ የውጭ ኃይሎች አሊያም በሰላማዊው የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ተወዳድድረው የከሰሩ ፖለቲከኞች መኖራቸውን ነው፡፡

ምንም እንኳን የአክራሪነት አስተሳሰብ እንዳይስፋፋ በአሁኑ ወቅት ሀገራችን እያስመዘገበችው ያለችው ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ለችግሩ ተጋላጭ እንድንሆን የሚያደርጉንን ድህነትንና ኋላቀርነትን ደረጃ በደረጃ እየቀረፈ ቢሆንም፤ ሰርቶ ማግኘት የሚቻል የማይመስላቸው አንዳንድ ግለሰቦች የአክራሪነት እምነትን ያልደከሙበት የገቢ ምንጭ በማሰብ ገንዘብ የሚያገኙበትን አንድ መንገድ አድርገው መተለማቸው አይቀርም፡፡ በእነ ሐሰን ጃርሶ የክስ መዝገብ ላይ በምስክርነት የቀረቡት የአቃቤ ሕግ እማኞች “ግለሰቡ ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶች በየወሩ ሁለት መቶ ዶላር ይቀበላል” በማለት ቃላቸውን የሰጡት ይህን ዕውነታ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ “ተጠርጣሪዎቹን በገንዘብ የሚያግዟቸው እነማን ናቸው?” የሚል ጥያቄን ማንሳት ይቻላል፡፡ ታዲያ የጥያቄውን ምላሽ እንዲህ ማየት ነው፡፡ ...

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት፤ ለእነ ሐሰን ጃርሶ ዓይነት ፅንፈኛ አክራሪዎች ከውጪ ገንዘብ የሚልኩ ሰዎች በሁለት የሚከፈሉ ናቸው፡፡ በአንደኛው ጎራ የሚካተቱት የሀገራችንን ነፃ እድገትና ልማታዊ ግስጋሴን ማየት የማይሹ የውጭ ሀይሎች በሃይማኖት ሽፋን የሚነግዱና ውጭ ሆነው በርቀት መቆጣጠሪያ /Remot Control/ የሀገር ውስጥ ፖለቲካን መዘወር የሚመኙ የቀቢፀ-ተስፈኞች ሰብሰብ ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ እስልምናንና ክርስትናን በማስፋፋት የራሳቸውን ፖለቲካዊ ግብ ማሳካት የሚሹ የውጭ ሃይሎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እርግጥ ሉዓላዊ መብቱ እንደ ተረጋገጠ ህዝብ የራሳችንን መብቶች ራሳችን ብቻ እንድንወስን፣ ሰላማዊና የተረጋጋ ህይወት እየኖርን በተፈጠረው የዕድገት ግስጋሴ ራሳችንን ጠቅመን የሀገራችን ልማት አጋር እንድንሆን፣ ከውጭ የሚመጡ ኢንቨስተሮችና ቱሪስቶች ለልማታችን አጋዥ እንዲሆኑ ከፈለግን፤ በእነዚህ ኃይሎች የገንዘብ ድጋፍ የሚታገዙ ግለሰቦችን በንቃት ልንከታተላቸው ይገባል፡፡

ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እየተገነባ ባለበት ሀገር ውስጥ የምንኖር ዜጎች እንደ መሆናችን መጠን፤ ይህኛው ወይም ያኛው ሀይማኖት በሃይል እንዲጫንብን መፍቀድ ያለብን አይመስለኝም፡፡ ሃይማኖት የግል እንጂ የጋራ ባለመሆኑ፤ ምርጫው ለተከታዩ መተው ይኖርበታል። በዴሞክራሲያዊ እሳቤ ውስጥ ለግለሰብ መተው የሚገባው ሃይማኖታዊ ምርጫ መንግስትም ሆነ ሌሎች ሃይሎች ጣልቃ እንደማይገቡበት በመገንዘብ፤ ሰላማችንን የሚያደፈርሱ የውጭ ጣልቃ ገብነቶችን አጥብቀን መኮነን ይገባናል፡፡

የእነ ሐሰን ጃርሶ ያልተሳካ እንቅስቃሴን ክስተት ብቻ ብንመለከት፤ ሀገራችን ያለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ የማያመላክትና ገፅታችንን የሚያጠለሽ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው ሀገራችን ተዓምራዊ በሚባል የለውጥ ሂደት ውስጥ ትገኛለች፡፡ ይህ ለውጥ ከ85 በመቶ በላይ የሆነውን የሀገራችን አርሶ አደር ህይወት እየቀየረ መሆኑን የሌሎች ሀገራት መሪዎች እንኳን ሳይቀሩ ምስክርነታቸውን እየሰጡ ነው፡፡

*የቅርቡን ለመጥቀስ ያህል ከመሰንበቻው አሜሪካ- በካምፕ ዴቪድ ውስጥ በተካሄደው የቡድን -8 ሀገሮች ጉባኤ ላይ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ኢትዮጵያ ውስጥ የአርሶ አደሮች ህይወት መለወጡን በመጥቀስ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ያላቸውን አድናቆት መግለፃቸውን እንደ አብነት ልናወሳው እንችላለን፡፡*

*ይህም ቀደም ባሉት ስርዓቶች በረሃብና በተመፅዋችነት የምንታወቅበትን ገፅታችን ዛሬ በልማታዊ መንግስታችን እየተቀየረ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ መልካም ነገር ፊፅሞ የማይዋጥላቸው ተቃዋሚዎች እንኳን ሳይቀሩ ሊክዱት በማይችሉበት ደረጃ ሀገራችን በሁሉም መስኮች በመለወጥ ላይ መሆኗን እያመኑ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን በማግኘት ላይ የሚገኘው ስኬታችን እንዳይታይ የሚፈልጉ ሃይሎች የሉም ማለት አይደለም፡፡*

*ታዲያ የእነ ሐሰን ጀርሶ ዓይነት ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ ግጭት የመቀስቀስ ቀቢፀ-ተስፋ እሳቤ ለእንዲህ መሰሎቹ የሀገራችንን መሻሻል የማይፈልጉና በየጊዜው የማያባራ የማጥላላት ዘመቻ ለሚያካሂዱብን ኃይሎች “ደስታ” መሆኑ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ስለሆነም ሃይማኖትን ተከትሎ ሊከሰት የሚችለውን የአክራሪነት አደጋን በመመከት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ፊት አንገታችንን ቀና አድርገን መሄድ የጀመርነውን አዲስ ጉዞ ለማጠናከር ሁላችንም እንደዜጋ መረባረብ ያለብን ይመስለኛል፡፡*

*ዛሬ ሀገራችን ከራሷ አልፋ ለአፍሪካ ሰላም ከፍተኛ አስተዋፅኦ የምታበረክትና አስተማማኝ ሰላም የነገሰባት ሀገር መሆኗ በገሃድ እየታወቀ፤ በረባ ባልረባው የሃይማኖት ንትረክ ጊዜያችንን የምናባክን ከሆነ፤ መረጋጋታችን እንቅፋት ሊገጥመው ከመቻሉም ባሻገር በገፅታችን ላይ ጥላሸት መቀባቱ አልቀረም፡፡ ይህም የውጭ ኢንቨስትመንት የመሳብ ዕድላችንን የሚያጠብ እንዲሁም የቱሪስት ፍሰትን ሊቀንስ ይችላል፡፡ እንግዲህ የእነ-አልሸባብ ቅርንጫፍ የሆኑት እነ ሐሰን ጀርሶ እንቅስቃሴ መቼም ሊሳካላቸው አይችልም እንጂ፤ ቢሰምርላቸው ኖሮ ተግባራቸው እነዚህን ጥቅሞቻችንን የሚያስቀር ከመሆኑም በላይ፣ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ “የሰላምና መረጋጋት ደሴት” እየተባልን የምንጠራበትን ሰናይ ስማችንን የሚያጎድፍ ይሆን ነበር፡፡*

*እርግጥ ተጠርጣሪው ግለሰብን የመሳሰሉ ፀረ-ሰላም ኃይሎችና የውጭ አክራሪ ተላላኪዎች በየሃይማኖት ተቋማቱ ውስጥ ሰርገው የገቡ አሊያም ለመግባት የሚሹ ሐሰተኛ መሲሆች የሉም አይባልም፡፡ እንዲያውም ቤተክርስቲያንንና መስጊዶችን የፖለቲካ መድረክ ለማድረግ በርካታ ጥረት ማድረጋቸው አይቀርም፡፡ በቅርቡ በህዝበ ሙስሊሙ ፍትሐዊ ጥያቄዎች ዙሪያ የሙስሊሙን አግባብ ያላቸውን ጥያቄዎች እየጠመዘዙ ለራሳቸው ፖለቲካዊ ፍጆታ ለማዋል የሞከሩ ጥቂት “የአመፅ ወኪሎች” ከዚህ አኳያ በአስረጅነት የሚታዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች በተለያዩ መንገዶች ጥቅማቸው የተነካ እንዲሁም አክራሪ ኃይሎች ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆን የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ ይህ ማንነታቸውም መንግስት ሃይማኖታዊ መብቱን ለጠየቀው ሙስሊሙ ማህበረሰብ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ተከትሎ በሰጠው ምላሽ አማካኝነትን ሊጋለጥ ችሏል፡፡*

*ታዲያ እነዚህና ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ሁኔታዎች ዛሬም ቢሆን በሀገራችን የአክራሪነት አደጋ የለም የሚያስብል አይደለም– በተለይም ከአል-ሸባብና ከአል-ቃዒዳ ጋር በተያያዘ ሁኔታ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ*

ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘው የእነ ሐሰን ጃርሶ የአል-ቃዒዳ ሴል የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ሃቅ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዳችን እስከ አሁን ስናደርግ እንደነበረው ሁሉ፣ ሃይማኖት የግል ሀገር የጋራ መሆኑን ተገንዝበን በልዩነት ምክንያት "ጅሃድ" በሚል የፖለቲካ ስልጣን ጥያቄን መመከት ይኖርብናል፡፡

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት እነ ሐሰን ጃርሶ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ላይ ውጊያ የሚከፍቱት ምቹ የሆነ ምህዳር አለ ማለት አይቻልም፡፡ ለምን ቢባል፣ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖትና መንግስት እንዲሁም መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ከመሆናቸውም በላይ፣ በዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ ፓለቲካዊ ፍላጎትን ማሳካት የሚቻለው በፖለቲካዊ ምህዳር እንጂ፣ ሃይማኖትን አስታክኮ ባለመሆኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከሽብር ተጠርጣሪው የእምነት ቃል በስተጀርባ የምንገነዘበው ሃቅ ቢኖር፣ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ የአክራሪነትና የሽብርተኝነት አደጋ እንደ ማንኛውም ሀገር ሊኖር የሚችልበት ነባራዊ ሁኔታ ቢኖርም፣ በሰላም ወዳዱና መቻቻልን መርሁ ያደረገው የሀገራችን ህዝብ ከፀጥታ ኃይሎች ጋር ተቀናጅቶ በሚያከናውናቸው ተግባራት ፍላጎቱ እንደ አመጣጡ የሚከስም መሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ዛሬ በፈጣን የዕድገት ባቡር ላይ የተሳፈረው ሥራ ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠቃሚነቱን ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ እያረጋገጠ ስለሆነ፣ ለከሰሩ ፖለቲከኞችና ሃይማኖትን እንደ ንግድ ለሚቀጥሩ ውህዳኖች ቦታ ሊሰጣቸው ስለማይችል ነው፡፡